# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ሚያዚያ 22 ቀን 2000 ዓም
**(May 1 2008)**

## ዓለም አቀፍ የሠራተኞች ቀንን በተመለከተ የተሰጠ መግለጫ

## እሪ በይ ምድሪቱ--መብቱን ይጠይቃል ዛሬም ላብአደሩ

የሰራተኛውን ሕዝብ መብት ለማስከበር የሥራ ሰዓት ገደብ ይደረግለት በሚል ጀምሮ የቀጠለው በዓለም አቀፍ ደረጃ የላባደሮች ቀን ሲከበር ከመቶ ህምሳ ዓመት ያለፈው ቢሆንም በሀገራችን ግን ይህ ቀን ሊከበር የ ለው ከመራራ ትግል በኋላ በዘመነ ደርግ እንደነበር የሚታወስ ነው፡፡ ሰርቶ አደሩ ሕዝብ ለመብቱ ያካሄደውን ክቡር ትግል ለታሪክ በሚገባ ዘርዝሮ ለዘንድሮውና ለመጪው ትውልድ ማሳለፍ ተገቢ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ከአበራ ገሙ እስከ ማርቆስ ሀጎስ፥ ዳሮ ነጋሽና ሌሎችም የስንቱን ጀግናና ቆራጥ ህይወት የጠየቀው ይህ ሕዝባዊ ትግል ሁሌም የላባደሩን የደም ግብር ጠያቂ ሆኖ እስካዛሬ መቀጠሉ ደግሞ የሀገራችን ክስተት ነው፡፡ የሀገራችን ምድር ዛሬም እሪ ስትል የሚፈሰውን የላባደር ደም የነጎድጓድ ጩኸት በማዳመጧ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ የላባደሩ ቀን ሲከበር ተሰልፈው የተጨፈጨፉትን የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎችን ስንዘክር በዚያውም ይህ ድርጅት ታሪኩና ተልዕኮው ከላባደሩና አርሶ አደሩ ሕዝብ ጋር እንደነበረና እንደሆነም ሳንጠቅስ ማለፍ አንችልም፡፡

የኢትዮጵያ ላባደሮች በማህበር ደረጃ ተደራጅተውና ተሰባሰብው መብታቸውን ለማስከበር ሲነሱ የአፄው መንግስት ሊያግዳቸው ብዙ የጣረ ቢሆንም አስፈላጊውን መስዋዕትነት በመክፈል በኢትዮጵያ ሠራተኞች አንድነት ማህበር (ኢሠአማ) ደረጃ በመላ ኢትዮጵያ ሊደራጁ ችለዋል፡፡ ሥርዓቱ የሠራተኛውን ትግል ለማፈን ወይም ለማሽመድመድ ባደረገው ጥረት የማህበሩን የተወሰኑ መሪዎች ከመግዛቱ ሌላ የበላይ ጠባቂው በነበረው በአሜሪካ በመታገዝ ኢሠአማን ከአሜሪካን የሠራተኛ ማህበሮችና ከሲአይኤ የስለላ ተቋም አስመሳይ ማህበራት ጋርም አቆራኝቶት ነበር፡፡ የየካቲት አብዮት ሲፈነዳ ሠራተኛው ከሰፊው ሕዝብ ጎን በመሆን ሲታገል በመጀመሪያ ግን ማህበሩን ማስመለስና ነፃነቱን ማስከበር ወሳኝ በመሆኑ የሠራተኛውን ጥቅም አሳልፈው የሰጡትን አስወግዶ ታጋይና ታማኝ መሪዎቹን ሰይሟል፡፡ በየካቲት 66 ሰራተኛው ዋና የትግል መሳሪያው የሆነውን የስራ ማቆም አድማ በአጠቃላይ አድማ ደረጃ ዕውን አድርጎ አብዮቱ በመሀል እንዳይቋረጥ ወይም እንዳይቀጭ ከፍተኛ አስተዋፅዖንም አድርጓል፡፡ ራሳቸውን ደርግ ያሉ ምርጥ መኮንኖች የሕዝብን ድል ቀምተው አብዮቱንም ሊቀብሩ ሲነሱ በተካሄደው መራራ ሕዝባዊ ትግል ላባደሩና ኢሠአማ ግንባር ቀደም ሆነው ታግለዋል፡፡ ኢሠአማ ልዩ ልዩ ጉባዔዎችን አካሂዶ በዴሞክራሲና በሀገሪቷ ዋና ዋና ጥያቀዎች ላይ ተገቢውን ውሳኔ ማሳለፍ ብቻ ሳይሆን በገቢርም በትግሉ ተሰልፎ መስዋዕትነትን ከፍሏል፡፡ መሪዎቹ እነማርቆስ ሐጎስ በፋሺስቱ ደርግ ተደብድበውና ተሰቃይተው ተረሽነዋል፡፡ በየፋብሪካው አያሌ ላባደሮች ሲታገሉ ረግፈዋል፡፡ በኢላአማ ደረጃም ሆነ በኢሕአፓነትም በትግሉ ላባደሮች ተሳትፈው የፖለቲካና የኤኮኖሚ ጥያቄዎችን በማንሳት ይጠበቅባቸው የነበረውን የትግል ሚናም በሚገባ ተጫውተዋል፡፡ ራሱን የሰርቶ አደሩ መንግስት ሲል የነበረው አረመኔ አገዛዝ ፀረ-ላባደር ስለነበር፥ የላባደሩን ማህበርና መሪዎች በከፍተኛ ደረጃ ጎድቶ ለፀረ ሕዝብ ወያኔ ሰለባ አድርጎታል፡፡

ሁሉም አምባገነናዊ አገዛዝ የሕዝብን ነፃ ድርጅቶች--በተለይም የላባደሩን--መቆጣጠርና ማፍረስ ዋነኛ ተልዕኮው ነውና ወያኔም የላበደሩን ትግል ለማፈን የራሱን ተለጣፊ የላባደሮች "ማህበር" ለመመስረት በተጣጣረበት ወቅት ላባደሩ መስዋዕትነት እየከፈለ ታግሎታል፡፡ ወያኔም የላባደሩን ማህበር አፍርሶ የራሱን ተለጣፊ ህጋዊ ብሎ ከመሰየም ወደኋላ አላለም፡፡ ዛሬ ዴሞክራሲ ጠፋ ከሚለው አንስቶ እስከ ብዝበዛ የኑሮ ውድነት ያሉትን ጥያቄዎች ሁሉ ስናጤን የኢትዮጵያ ላባደሮች ትግላቸው ገና ድልን ጠባቂ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ የወያኔ አገዛዝ

ላባደሩን በብሄረሰብና በሃይማኖት ለመከፋፈል፤ በጥቅማ ጥቅም በጣት የሚቆጠሩትን ደልሎ የላባደሩን ህብረትና ትግል ለማፈን ሳይሰለች እየሰራ ነው:: ብዙ ሺህ ሰራተኞች ከሥራ ተባረዋል:: በነፃ ገበያ ስም የወያኔ አገዛዝ ራሱ የኤኮኖሚውን ቁልፍ ቁልፍ ቦታ ይዞ መረን አልባ ብዝበዛውን አስፍኗል:: የዛሬው የሰራተኛ ህግ እንዳለፈው አገዛዝ ሁሉ የባርነት ህግ ከመሆን አላለፈም:: የኑሮ ውድነት ጣራ ሰብሮ ሲመጥቅና ሰፊው ሕዝብ ለመከራ ሲዳረግ ላባደሩ ሊከላከል የሚችልበት ሁኔታ ተጣቦና ታፍኖ ይገኛል:: ጥቅሙን አሳልፈው የሰጡ በላዩ ላይ ተሰይመውበት ለአገዛዙ በማገልገል ትግሉን አዳክመዋል:: የዘንድሮውም የዓለም ሠራተኞች ቀን በኢትዮጵያ የሚከበረው የህገራችን ላባደሮች ዕጣ ከአስከፊም በላይ አሰቃቂ  በሆነበት ሁኔታ ነው:: ኢሕአፓ ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከዛሬ ከዓላማዎቹ አንዱ አርጎ የቆመለት የላባደሩ መብት መከበር ጉዳይ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠውና የሚታገልለትም ነው:: በአጠቃላይ የዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብት በሀገራችን መከበር ባሻገር በተለይ የላባደሩ በነፃ የመደራጀትና ይህም በየትኛውም ዓይነት የፖለቲካና ኤኮኖሚያዊ ሥርዓት የማይገሰስ መብት መሆኑን ኢሕአፓ አጥብቆ ያምናል:: የላባደሩ ኤኮኖሚያዊ መብቱ መከበር ከዚህ የላባደሩ የፖለቲካ መብት መከበር ጋር በጥብቅ የተቆራኘም መሆኑን መገንዘቡ ተገቢ ነው:: ኢሕአፓ ይህንን ሲል፥ ላባደሩ አለአግባብ ከሥራ ገበታው ተፈናቅሎ መንገድ ላይ እንዳይጣል፥ አሰሪዎች በጋራ ተጥቀናጅተው ገበያውን ለመቆጣጠር የምርቶቻቸውንና የሸቀጦቻቸውን ዋጋ እንደፈለጋቸው በመተመን ላባደሩና ሠራተኛው በኑሮ ውድነት ኑሮው እንዳይመሰቃቀል፤ ለጤንነቱ አደገኛ በሆነ የሥራ ቦታ የደህንነት ዋስትና የማግኘት ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠርለት፤ ሠራተኛው ያልተካፈለበት ሕግን በማውጣት ለጭፍን ብዝበዛ እንዳይጋለጥ፤ ለሚሰጠው የሙያና የጉልበት አገልግሎት ተገቢውን ክፍያ እንዲያገኝ የሚያስችለውን ሕግ/ሥርዓት በነፃ ማኅበሩ አማካይነት የሚደራደርበት፥ የሚዋዋልበት፤ ለህሊናው መታደስ፥ ለተሟላ ጤንነቱ፥ ለቤተሰቡ የሚሆነው ተገቢ የእረፍት (ሳምንታዊ፥ ዓመታዊ...)ቀናት እንዲኖረው፤ የጡረታ መብቱ እንዲከበር፤ ባጭሩ በተወሰነ የታሪክ አጋጣሚም ሆነ በሥርዓት ተመርጠው ሥልጣን ላይ የሚመጡ ሁሉ መብቱን አላግባብ እንዳይደፈጥጡና ማኅበራዊ ኢፍትሃዊነት እንዳይደርስበት ለሚያረገው ትግል፥ አሁንም እንደቀድሞው ከጎኑ ቆሞ እንደሚታገል ዳግም ያረጋግጣል ለማለት ነው:: የወያኔ ፀረ-ሕዝብ አገዛዝ የኢትዮጵያን ሠራተኛ ሕዝብ ከበደል በላይ በደልና መከራ ጭኖበት እያሰቃየው ስላለም ትግሉ በጋራ ለዚህ ሁሉ የሠራተኛው መብት ጭምር መከበር መታገልን ይጠይቃል::

በመሆኑም የዓለም አቀፍ የሠራተኛውን ቀን ስናከብር ለተፋፋመ ትግል ድርጅታዊ ዝግጅታችንን ለማጠናከር ቃል በመግባትና በረጅሙ የላባደሩ ትግል ዘመን የፈሰሰውን ደምና የተከፈለውን መስዋዕትነት ሁሉ በመዘከር ነው::

የኢትዮጵያ ላባደሮች ትግል ድልን ይቀዳጃል!!
ኢሕአፓ የላባደሩ ትግል አጋር ነው!!

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France